ቁጥር: ______________________
Ref. No
ቀን: ______________________
Date

**ለክቡር የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር**
**ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)**
**<u>አዲስ አበባ</u>**

**ጉዳዩ፡- <u>"አላግባብ የተፈረደበት" ባልደረባችንን መንግሥት "ነፃ እንዲያወጣው" ስለመጠየቅ፡-</u>**

በኢትዮጵያ ዜጎች ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለማዋለድ ዘመናትን የተሻገረ መሪር ተጋድሎ ማድረጋቸው ይታወቃል፡፡ ከነዚህ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን አዋልዶ "ዳዴ" ለማስኬድ ብርቱ ትግል ካደረጉ የማኅበረሰብ ክፍሎች መካከል ደግሞ የነጻው ፕሬስ አባላት ቀዳሚ ረድፈኛ ሆነው ይጠቀሳሉ፡፡ ነጻው ፕሬስ ላለፉት ከሃያ ለሚልቁ ዓመታት ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ፣ የዜጎች መብት ያለመሸራረፍ እንዲከበር ባካሄደው ትግልም በርካታ ጋዜጠኞች ለአሳዛኝ ዕስርና እንግልት፣ ብሎም ለከፋ ስደትና ለዘግናኝ ሞት ተዳርገዋል፡፡ በተለይም ከምርጫ 97 በኂላ ግልጽ ሆኖ የመጣው መንግሥታዊ የዕመቃ ፖለቲካ፣ ከከፋው ስደትና ዕስር የተረፉት ጥቂት የነጻው ፕሬስ ውጤቶች ሲያደርጉት በቆዩት ትግል ላይ ግዙፍ መከራን የጋበዘ ነበር፡፡ ፕሬሱን ባለበት ለማዳከምና በሂደትም ለማክሰም ታስቦ ይፈጸም የነበረው ይህ መዋቅራዊና ስልታዊ ጥቃት ከባድ በመሆኑም፤ የአፈና በትሩን ተቋቁሞ ለመዝለቅ የሚቻል አልሆነም፡፡

በዚህም ምክንያት በ2006 ዓ.ም በአምስት መጽሔቶችና አንድ ጋዜጣ ላይ "ሕገ መንግሥቱን በኃይል ለመናድ"፣"የሻዕቢያን የሽብር ተልዕኮ ለማስፈጸም" እና "ከመጽሔት (ጋዜጣ) ተገቢውን ገቢ ባለማስገባት (ግብር በማጭበርበር)" የሚሉ፣ ተለምዷዊ የሆኑ የፈጠራ ክሶችን በማዘጋጀትና በመንግሥት የብዙኃን መገናኛዎች ጭምር የዘመቻ ደቦ በመክፈት፣ ጋዜጠኞችና አዘጋጆች ከሀገር እንዲሰደዱ ተደርጓል፡፡ በወቅቱ የዕስር ማስፈራሪያው ደርሷቸው ከነበሩት ጋዜጠኞችና አዘጋጆች መካከል፣ የሚመጣውን ለመቀበል ሲል በሀገር የቀረው ብቸኛው ተከሳሽ የዛሬዋ "ግዮን" የወቅቱ "ዕንቁ" መጽሔት ማኔጂንግ ዳይሬክተር ፍቃዱ ማኅተመወርቅ ብቻ ነበር፡፡

ጋዜጠኛ ፍቃዱ ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ በኢትዮጵያ ነጻ ፕሬስ ውስጥ ከአዘጋጅነት እስከ አሳታሚነት በተለያዩ የሙያው እርከኖች፣ ሢሠራ የቆየ፤ ዜጎች ለሃሳብ ነጻነት የሚያደርጉትን ትግል ከድብደባ እስከ ዕስራት ድረስ በየደረጃው ዋጋ በመክፈል፣ ለሙያው የታመነ ጋዜጠኛ ነው፡፡ ከመጋቢት 2010 ዓ.ም በኂላ በሀገሪቱ ላይ የመጣውን የለውጥ አየር ተከትሎም እርሱና በርካታ የሙያ አጋሮቹ ለኹለት አሥርታት "ቤተሰቤን ኑሮዬን" ሳይሉ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን እውን ለማድረግ የከፈሉትን ዋጋ ታሳቢ በማድረግ፤ "ግዮን" የተሰኘች መጽሔት በማቋቋም፤ የተከሰተው ለውጥ ተቋማዊ ሆኖ፣ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት እስከ ወዲያኛው

እንዲከበር ለማስቻል፣ ወትሮ የነበረውን የነጻው ፕሬስ የትግል ሚዲያ ቅርጽ ወደ ሙያዊ (Professional) ሚዲያነት ከማሻገር በተጨማሪ ሚዛናዊ ዘገባን በማቅረብ፣ በሀገር ውስጥና በውጪ ይኖሩ የነበሩ ኢትዮጵያዊ ምሁራን፤

ማለትም፡-

- አምባሳደር ዶ/ር ካሳ ከበደ
- ፕ/ር ሕዝቅያስ አሰፋ
- ፕ/ር መሳይ ከበደ
- ፕ/ር ጌታቸው በጋሻው
- አቶ ተረፈ ወርቁ

እና ሌሎችም በጽሑፍ አቅራቢነት ማኅበረ-ፖለቲካዊ ችግሮቻችንን ሊፈቱ የሚያስችሉ ገንቢ ሃሳቦችን እንዲያዋጡ ዕድሉን በመስጠትም ሆነ መድረኩን በማመቻቸት (በግዮን መጽሄት ዕትሞች በግልጽ ሰፍሮ እንደሚነበበው)፤ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን የተቀዳጁትን ለውጥ ወደላቀ ተቋማዊ ድል ለማሻገር የበኩሉን ሚና ለመወጣት እየታተረ የሚገኝ ጋዜጠኛ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ኢትዮ ሐበሻ የተሰኘ ጋዜጣ አቋቁሞ ለውጡን በሙያው ለማገዝ ለሚመለከተው መንግሥታዊ መ/ቤት አመልክቶ ምላሽ በመጠበቅ ላይ ይገኝም ነበር፡፡

ይሁንና ከዓመታት በፊት የነበረውን ጨቋኝና በዝባዥ ሥርዓት ለመጣል ነፍጥ አንስተው "ዱር ቤቴ" ካሉ የፖለቲካ ቡድኖች አንስቶ፣ በግፍ ዕስር ላይ እስከቆዩት ጋዜጠኞችና ፖለቲከኞች ድረስ፤ ብሎም በተለያዩ "ወንጀሎች" ተከስሰው ሀገር እንዳይገቡ ዕገዳ እስከተጣለባቸው ግለሰቦች ድረስ፣ በይቅርታና በኋላም በተቋቋመው የምህረት ቦርድ ነጻ እንዲሆኑ ትልቅ ተግባር ቢከወንም፣ ከፍ ሲል በተጠቀሰው እና ፕሬሱን ለማፈን ሆን ተብሎ በተፈበረከው ክስ ሰለባ በነበረው ብቸኛው ቀሪ ጋዜጠኛ ፍቃዱ ማኅተመወርቅ ላይ የተከፈተው መዝገብ እንዲቀጥል ተደርጎ፣ "ህገወጡ ክስ" እንዲቋረጥለት ደጋግሞ ያቀረበው ጥያቄም "ሰሚ አጥቶ"፣ ያለፈው ስርዓት "ውርስ" በሆነው የክስ መዝገብ "ጥፋተኛ" በሚል የሰባት ዓመታት ዕስር እንዲበየንበት መደረጉ ሁላችንንም ያስደነገጠ ሆኗል፡፡

**ክቡርነትዎ፡-**

በሚሊዮን በሚቆጠሩ ብሮች የሀገር ሀብት መዝብረው፣ በሙስናና ግብር ማጭበርበር ታስረው የነበሩ ግለሰቦች ሳይቀሩ ለውጡን ተከትሎ በተቸራቸው ምህረት፤ ሰላማዊ ህይወታቸውን ለመኖር ዕድል ባገኙበት በዚህ ወቅት፤ ለዴሞክራሲና ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት መረጋገጥ ሲባል፣ ስርጭቷ ከአዲስ አበባ መሻገር ባልቻለችው ዕንቁ መጽሔት ላይ በ2006 ዓ.ም በ"መቶ ሺኅዎች" በሚቆጠር "የሀገር ውስጥ ገቢን ማጭበርበር" በተባለ "ፍጹም የፈጠራ ክስ" የሰባት ዓመት ዕስር መበየኑ ሁላችንንም ከማሳዘኑ ባሻገር፣ ለበርካታ ዓመታት በእንግልትና ሞት ዋጋ የከፈልንለት ለውጥ "ወዴት እየሄደ ነው?" ብለን እንድንጠይቅም ያስገደደ ሆኖብናል፡፡

ከወረቀት ዋጋ ንረት፣ ማተሚያ ቤት ውድነትና ስፖንሰር ሺፕ ክልከላ ድረስ፤ የፋይናንስ ድጋፍ አጥቶ ብቻውን እየተንገዳገደ ዓመታትን ለዴሞክራሲያዊ ትግሉ ግብ መምታት በኪሳራ ሲንቀሳቀስ ለቆየው ነጻው ፕሬስ፣ በመቶ ሺህዎች በሚቆጠር ገንዘብ የግብር ማጭበርበር መክሰስ በጊዜው ትልቅ ስላቅ ቢሆንም፤ ክሱ ተንከባሎ በለውጡ ማግስትም ጸንቶ መቀጠሉ ግን፣ ትናንት መራር ዋጋ ከፍለው "የነጻነት አየር እየተነፈስን ነው" ለሚሉት የነጻው ፕሬስ አባላትም ሆነ፤ በተከፈተው የነጻነት ዐውድ ምክንያት የሚወዱትን ሙያ ለመቀጠል ሻንጣቸውን ላነገቡ ስደተኛ ጋዜጠኞች ያልተገመተ ዱብዳን የፈጠረ ነው፡፡

**ክቡር ጠ/ሚኒስትራችን፡-**

እኛ ሥምና ድርሻችን ከታች የተዘረዘረ የግዮን መጽሔት አባላት፣ ጉዳዩ የሚመለከታችሁ የመንግሥት አካላትና የለውጡ አመራሮች፤ ይህንን ከአምስት ዓመታት በፊት ነጻውን ፕሬስ ለመድፈቅ በፈጠራ ተሰናድቶ፣ ዛሬ ላይ ውሳኔ ያገኘ "ፍርድ" በመሻር (በማቋረጥ) ባልደረባችንና የመጽሔታችን ማኔጂንግ ዳይሬክተር ፍቃዱ ማኅተመወርቅ ነጻ ወጥቶ ዕድሜ ዘመኑን ዋጋ የከፈለለትን ብሎም የሚናፍቀውን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የመገንባትና ለውጡን ተቋማዊ የማድረግ ህልሙን እውን እንዲያደርግ የበኩልዎን ሐላፊነት እንዲወጡ በማክበር ስንጠይቅ፤ ሀገራችን ዛሬ ላይ በአንጻራዊነት ለተጎናጸፈችው የሚዲያ ነጻነት፣ የከፈላችሁትን ዋጋ በመረዳትም ሆነ ያላችሁን ቀናዒነት በመተማመን ጭምር እንደሆነ በትህትና ለመግለፅ እንወዳለን፡፡

**"ከአክብሮት ሠላምታ ጋር"**

ሮቤል ምትኩ (የግዮን መጽሔት ዋና አዘጋጅ)
ኄኖክ ገለታው (የግዮን መጽሔት ማኔጂንግ ኤዲተር)
አለማየሁ ባዘዘው (የግዮን መጽሔት ከፍተኛ አዘጋጅ)
ብሩክ መኮንን (የግዮን መጽሔት አዘጋጅ)
ሙሉጌታ አክሊሉ (አዘጋጅ)
ፍቅርተ ተሾመ (አዘጋጅ)
ሁሴን ከድር (አምደኛ)
ሠላም ግርማ (ጸሐፊ)

"መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን!"

**ግልባጭ፡-**
*ለምክትል ጠ/ሚ/ር አቶ ደመቀ መኮንን
*ለጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት ፕሬስ ሴክሬተሪያት
*ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የህግ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ
*ለጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት
*ለብሮድካስት ባለስልጣን
*ለኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን
*ለአገር ውስጥና የውጭ ሚዲያዎች በሙሉ

ለበለጠ መረጃ፡- 0911612793 / 0911101604